# ለዘኀለፈ ሥርየት ወለዘይመጽእ እቅበት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ::

«የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ግማደ መስቀል ያስመጣውን ዓፄ ዳዊትን በቅሎ ረግጣ ገደለችው ሲባል ቅር ያሰኛል፤ ታሪክ ንም ያቀዘቅዛል::» /ብላታ ወልደጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ /. ሥነ ምግባር፣ ገጽ 58/

ድንገተኛ ክስተቶች ብዙ ጊዜ ታሪክን ያቀዘቅዛሉ:: አንዳንድ ጊዜ ማንነትንም ያሳጣሉ:: ከሦስት ሺ ዓመት በላይ እግዚአ ብሔርን በማምለክ፣ ዐሥራቱን በኩራቱን በማውጣት፤ መሥዋዕቱን በመሰዋት ሁለት ሺ ዓመቱንም ክርስቶስን በመስበክ፤ ፍቅርን በመስጠት፤ አገርን በመጠበቅና ሕዝብን በመምራት ታሪክ የሠራችው ቤተ ክርስቲያን መለያየት ገጠማት መባሉ ቅር ያሰኛል:: የነቢዩ መሐመድን መልእክተኞች ሳይቀር አክብራ የተቀበለች ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ልጆቿ ተወጋገዙ ተብሎ ሲነገር መስማት ያስደነግጣል፤ በእርግጥም እንዲህ ያለው ነገር ብላታ ወልደጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ እንዳሉት ታሪክን ያቀዘቅዛል:: ታቦተ ጽዮንን የተቀበለች፤ ክህነተ አሮንን መሥዋዕተ ኦሪትን ለአንድ ሺ ዓመታት የያዘች፤ በጌታችን ኪደተ እግር የተባረከች፤ ግማደ መስቀሉን የተከለች፣ ለተሥዓቱ ቅዱሳንና ለሌሎቹም ማረፊያ ወደብ የነበረች ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ልጆቿ በመለያየት ባዘኑ ሲባል ከመስማት በላይ ምን ቅር የሚያሰኝ ነገር አለ:: ከዚህስ በላይ ታሪክን የሚያቀዘቅዝ ምን ነገር አለ ?

የመለያየት ምንጭ ሰይጣን ቤተ ክርስቲያንን ለመበተን ዐርፎ አያውቅም:: ሰይጣን በትዕቢት፣ በዐመፅና በክህደት ራሱን ከጸጋ እግዚአብሔርና ከማኅበረ መላእክት እንደለየ ሁሉ አዳምንም ከእግዚአብሔር ለይቶት ነበር:: በኋለኛውም ዘመን ብዙ ጊዜ ልብ የሚከፍል ነገር እያመጣ ሐዋርያትን ከጌታ፤ እንዲሁም እርስ በእርሳቸው ሊለያያቸው ይፈልግ ነበር:: ማርያም ባለሽቶዋ የጌታን እግር በቀባች ጊዜ ይሁዳ «ይህ ሽቱ ተሽጦ ለድሆች ያልተሰጠው ስለምንድን ነው» ያለው ከጌታ በላይ ለድሆች ተገድዶላቸው ሳይሆን ሠላሳ ብር ቀረብኝ የሚል የተደበቀ ውስጣዊ ፍላጐት ስለነበረው ነው:: ጌታም የመለያየት ተንኰሉን ቢያውቅም ሰው ሆኖ የተገለጠው ለአርአያነትም ነውና «ለምቀበርባት ቀን እንድትጠብቀው ተውአት . ድሆችስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና . እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም» በማለት መለሰ እንጂ «ሌባ» ስለሆንክ ነው ብሎ አሳሳፈረውም:: ዮሐ. 12:1-7 ነገር ግን ሰይጣን ሁልጊዜም እንዲህ ዐይነት በተደባበቀና ዓለማዊ ፍላጐት ባልጠፋላቸው ሰዎች እያደረ መለያየትን እንዲያመጣባቸው ዐውቀው ይጠብቁ ዘንድ ለሐዋርያት በቅዱስ ጴጥሮስ በኩል «ስምዖን ሆይ . እነሆ ሰይጣን ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለአንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና» ሲል አስጠንቅቋቸዋል:: ሉቃ.22:31 ሰይጣን የምንጊዜም ደካሙ ይኸው ነው:: በረባውም ባልረባውም ብንከፋፈልለት ደስ ይለዋል:: እንዲህ ዐይነቱ መለያየት ደግሞ የእምነት መጥፋትንም ያስከትላል:: ጌታ «እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ» ሲል ለቅዱስ ጴጥሮስ የተናገረው ከእርሱ የሚከብር ሐዋርያ እንደሌለ ዐውቆ ሁሉም በመለያየት እምነቱን እንዳያጠፋ ለማስጠንቀቅ ነውና::

በዚህ ዓመት በቤተ ክርስቲያናችን ለተፈጠረው ውግዘት ምክንያት የሆነው በአሜሪካን አገር የተፈጸመው ሲመተ ኤ'ስ ቆጳሳት ነው:: የሾሙት አባቶች ስለሁኔታው ያቀረቡት ምክንያት ከላይ ካየነው የጌታ ትምህርት አንጻር ሲታይ ብቁ አይደለም:: በእርግጥ የተፈጠሩት ችግሮች እንደተባሉት ናቸውን? የሚለው ጥያቄ ከእውነትና ከታሪክ አንጻር ሲታይም ሚዛን አይደፋም:: መፍትሔውስ ይህ ነውን? የሚለውም ሲነሣ ብዙ አስቸጋሪ ነገሮች ይታያሉ:: «ወንድሞችህን አጽና» ተብሎ አደራ የተቀበለው የቅዱስ ጴጥሮስ ተከታዮች እንደቃሉ ቤተክርስቲያንን እያጸኑ ነው ወይስ በራሳቸው መንገድ እየሔዱ ጥንት የተሰደዱትስ ፈተናውን እንዴት ተወጡት? የሚለውንም ማየት ያስፈልጋል:: ቅዱስ አትናቴዎስ ከአምስት ጊዜ በላይ ከመንበሩ ተሰድዷል:: የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕጋዊ ትርያርክ ሆኖ እያለ በግፍ ተሰድዶና በመንበሩም ላይ አርዮሳዊ ተተክቶበት እንኳ እርሱ ወደ መንበሩ ለመመለስ ጊዜውን ጠበቀ እግዚአብሔርንም ተስፋ አደረገ እንጂ ሲኖዶስ አልመሠረተም፤ አንድም ኤ'ስ ቆጳስ አልሾመም:: በዘመኑ የነበሩ የሮማ አባቶችም የእርሱን ሕጋዊ ትርያርክነት መሰከሩለት እንጂ ሲኖዶስ እንዲመሠርት አልፈቀዱለትም:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም አውዶክስያ በግፍ ስታሳድደው ሕዝቡ እርሱን ስለሚወደው ጸብ ተነሥቶ ችግር እንዳይፈጠርና ቤተ ክርስቲያንም እንዳትከፈል ስደቱን በአኰቴት ተቀብሎ ሔደ . በዚያም አስተማረ አገለገለ እንጂ ሲመት ሰጥቶ ቤተ ክርስቲያኑን ከሁለት አልከፈላትም:: በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ካለፉት አባቶቻችን መካከል ስደትን ምክንያት አድርጎ እንዲህ ዓይነት ታሪክ የፈጸመ አባት የለም::

ለቤተክርስቲያን ስለአሁን ሁኔታዋ ብቻ ሳይሆን ስለወደፊት እጣ ፈንታዋም ከክርስቶስ በታች እንደ አባቶች ሊጨነቅላት የሚገባው አካል የለምና:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በገዛ ደሙ የዋጃችን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» የሚለው የአባቶች ሓላፊነት ከባድ በመሆኑ ነው:: ሐዋ. 8 ፈተናዎች እንኳ ቢመጡ እንዴት ማሳለፍ እንዳለባቸው፤ ከዚህም የተነሣ እውነተኛ መጋቢነታቸውን እንዳያስታጉሉ «....ከእይሁድም ሴራ በደረሰብኝ ፈተና ለጌታ እየተገዛሁ ዘመኑን ሁሉ ከእናንተ ጋር እንዴት እንደኖርሁ እናንተ ታውቃላችሁ፤ .....ከሚጠቅማችሁ ነገር አንዳች ስንኳ አላስቀረሁባችሁም» በማለት አብነቱን ገልጿላቸዋል:: ሐዋ. 20:20-22

# ለዘኀለፈ ሥርየት ወለዘይመጽእ እቅበት

በዕውቀት ከመበልጸግ የተነሣ ቢያደርጓቸው የማያስነቅፉ ነገሮች ቢኖሩ እንኳ ለማያውቀው መሰናክል የሚሆኑ ከሆኑ ይተዋሉ እንጂ «ብታውቅ ዕወቅ . ባታውቅ የራስህ ጉዳይ» ተብለው የሚፈጸሙ አይደሉም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በአንተ ዕውቀትም ይህ ደካማ ይጠፋል እርሱም ክርስቶስ የሞተለት ወንድም ነው። እንዲህም ወንድሞችን እየበደላችሁ ደካማም የሆነውን ኅሊናቸውን እያቆሰላችሁ ክርስቶስን ትበድ ላላችሁ። ስለዚህም መብል ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ ወንድሜን እንዳላሰናክለው ለዘላለም ከቶ ሥጋ አልበላም።» በማለት የገለጸው ይህንኑ ነው። እንኳን ብዙ ክርስቲያኖችን አንድንም ሰው የሚያ ሰናክል ነገር በሐዋርያትና በመምህራን ዘንድ የተናቀ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ መብላቱ የማያስነቅፈውን ሥጋ እንኳ ለመተው ከወሰነ አሁንስ ለቤተ ክርስቲያን ሲባል ብንተወው ምን አለ? በመለያየትስ የምንጠቀመው ማንን ነው? በርግጥ በዚህ ጊዜ ይህን መፈጸማችን ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ነውን? የሚለውን ሰናነሣ ደግሞ ከሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና ለቤተ ክርስቲያን ከማሰብ ይልቅ እልህ ጎልቶ ይታያል። የእልህ ፍጻሜው ደግሞ ፍላ ጐትን መከተል ነው። ፍላጐቱን የተከተለ ደግሞ መለየትን ያመጣል። «መለየትን የሚወድ ምኞቱን ይከተላል» ተብሏልና። ምሳ. 18:1

የመለያየት ውጤቱ ሁልጊዜም አንድና አንድ ነው፡ ይኸውም ጥፋት ብቻ ነው። «እርስ በርስዋ የምትለያይ መንግሥት ሁላ ትጠፋለች . እርስ በርሱ የሚለያይ ከተማም ሁሉ ወይም ቤት አይቆምም» ሲል ጌታችን አስተምሮናልና። ማቴ. 12:23 ዐሥሩ ሁለቱ ነገደ እስራኤል በሮብዓም ዘመን ከሁለት በመከፈላቸው ምክንያት ኀይላቸው ስለደከመ ጸጋቸውም ስለተገፈፈ ጠላት እየተነ ሣ አንድ ጊዜ ዐሥሩን ነገድ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሁለቱን ነገድ እየማረከ እያወረደ የመከራ ጽዋ ሲያጠጣቸው ኖረ። ከዚያ መለያየት በኋላ እስራኤል ለሁለት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ያህል ከመከራ ወደ መከራ እየተሸጋገረች ኖረች እንጂ ዕረፍት አላገኘችም። የአሁኑም ጠሷ የዚያው ውጤት ነው ማለት ይቻላል። ለዚህም ነበር ይህን አስቀድሞ የተመለከተው ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት «ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ሶበ ይሔልው አኀው ኀቡረ፤ እነሆ ወንድሞች /ውሉደ ያዕቆብ . እስራኤል/ በኅብረት ቢቀመጡ በአንድነት ቢኖሩ መልካም ነው» ሲል ምኞቱንና መለያየታቸውን አንድ አድርጎ የገለጸው። የፍልስጥኤሞች ባለቤትነትም መነሻው የእስራኤል መለያየትና ስደት ነው።

እስልምናን ለዚህ ያበቃውና በዓለም ላይ ያንሰራፋውም በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የተነሣው መለያየት ነው። ከኬልቄዶን ጉባኤ ጀምሮ የተፈጠሩት መለያየቶችን ተከትለው የሚመጡት መወጋገዞችና ሌሎች አላስፈላጊ ነገሮች ጠንካራ የክርስቲያን አገሮች የሚባሉትን ሰሜንና ምሥራቅ አፍሪካን፥ መካከለኛው ምሥራቅን ብቻ ሳይሆን አውሮፓና ሩቅ ምሥራቅንም ሳይቀር የችግሩ ሰለባዎች አድርጓቸዋል።

ከመለያየት በኋላ የሚታዩ አንዳንድ አላስፈላጊ ነገሮች ደግሞ ሁል ጊዜም ለጥፋት ትልቅ በር ከፋቾች ናቸው። የሮማ ካቶሊክ በኦርቶዶክስ ላይ የከፈተችው ዘመቻ እስልምናን እንደርድሮ ለማስገባት ታላቅ በርን ከፈተለት። የመስቀል ጦርነትን ተከትሎ በምሥራቅ ኦርቶዶክሶችና በኦሪየንታል ኦርቶዶክሶች ላይ የከፈተችው ዘመቻ ቤዛንታይንን ለቱርክነት፥ ቁስጥንጥንያንም ለኢስታንቡልነት አበቃቸው እንጂ ያተረፈው ትርፍ የለም። የእኛው የናግራን ዘማች አብርሃ ናግራንን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ እገዛለሁ ማለቱ አገሪቱን አገረ እስላም ከማድረጉና ለዘላለም እንድናጣት ምክንያት ከመሆን አላለፈም። ምን አልባትም አብርሃ ነገሩን በእርጋታ ይዞ ከእናት አገሩ ራሱን ሳይለይ ቢቆይ ኑሮ እስልምና የእነ ጠርጠሉስንና የእነ አውግስጢኖስን አገር /አሁን ሊቢያንና ቱኒዝያን/ ቀርቶ ግብጽንም ሳይነካት ይችል ነበር። የሩሲያ ካህናት በ1917ኙ ልብስ ይለበስ ወይስ ቢቀር በሚል ክርክር ሰምጠው እርስ በርሳቸው ተወጋገዙ፡ ይባስ ብለው የተወሰኑ ካህናት እና ጳጳሳት የሲኖዶሱን ውሳኔ ትተው የራሳቸውን ሐሳብ እንከተላለን በሚል ቤተ ክርስቲያኗን በጠበጥዋት። ይህም ሌኒን ማንም ሃይ ሳይለው የቦልሼቪክን አብዮት እንዲያቀጣጥል ብሎም ቤተ ክርስቲያኒቱን በእጁ አስገብቶ የ 70 ዓመት የመከራ ዘመን እንድትገፋ አደረጋት።

ካቶሊኮች ኢትዮጵያን በባልያን ለማስወረርና ቤተ ክርስቲያኒቱንም ግብሯን ለውጠው የራሳቸው ለማድረግ ያሰቡት መለያየትን በመፍጠር ነበር። ፊትለፊት ተከራክሮ መርታት ያቃተውና በትምህርቱ የአንድንም ሰው ልቡና መማረክ ያቃተው አልፎንዙ ሜንዴዝ ሁለት ደቀመዛሙርትን ቅባትና ጸጋ አድርጎ ለማሠልጠንና በሊቃውንቱ መካከል ክፍፍልን ለመፍጠር ግን አልተሣነውም ነበር። እንዳሰበውም መከፋፈሉ ይዞለት አገሪቱን በመሳፍንት እንድትከፋፈልና ታላላቅ አድባራትና ገዳማት ሳይቀሩ በቅባትና በጸጋ ትምህርት እንዲጥለቀለቁ አደረገ። በዚህ መለያየትም አገሪቱ አንድነቷን አጣች። የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትም በእጅጉ ተዳከመ። ሊቃውንቱን ጊዜያቸውን በክርክርና በመነቃቀፍ እንዲያጠፉት አድርጓቸዋልና። በዚህ ምክንያት በግራኝ አሕመድ የፈረሱትን ሙሉ በሙሉ መገንባትና መመለስ፡ የተበረዘውንም ባሕልና ትምህርት ማረም ቀርቶ እርስ በእርስ መደማመጥም ፈጽሞ ጠፋ። በዚህ ምክንያት እስካሁን ድረስ ቤተ ክርስቲያን የምትወቀስበት የሶማሌ፣ የደቡብና የምዕራብ ኢትዮጵያ ቦታዎች ጠፍና ምድረበዳ በመሆን ቆይተው ለእስልምናው ተመቻቹለት። ስለዚህም በምጽዋ ወደብና በሐረር የጀመረው የእስልምና ጭላንጭል መሐል አገር ዘልቆ ለመግባትና መስጊዱንም ለማስፋፋት በቃ። ይህ ብቻ አይደለም እጅግ ብዙ ጥፋቶች ደረሱ፣ በመለያየት ምክንያት።

አሁንም ቢሆን በቅን ኅሊናና በንጹሕ ልብ ቁጭ ብሎ ስለልጆቹ የሚጨነቅና የሚያስብ ወላጅ ካለ ከአሁኑ ጉዳይ በላይ አሳሳቢ ነገር ይገጥመዋል ለማለት ያስቸግራል። ማንንም ከመንቀፍና በማንም ላይ ከመፍረድ በፊት እንዲሁም ድርጊቱን ይዞ ከመሮጥ

# ለዘኀለፈ ሥርየት ወለዘይመጽእ እቅበት

ቆም ብሎ ደግሞ ደጋግሞ ማሰብን ይጠይቃል። «የሰነፍ አፍ ለራሱ ጥ ፋት ነው፣ ከንፈሩም ለነፍሱ ወጥ መድ ነው» እንደተባለ። ምሳ.18:7 ዙሪያችንን የከበቡን አማሊቃውያን፣ ዓይን ዓይናችንን የሚያዩትን ደቂቀ እስማኤል የሚያስቡትን እናውቅ ይሆን? ውሉደ ልዮንስ ምን እያዘጋጁልን ይሆን? መለያየታችን ለእነርሱ ምን ጊዜም ደስታ ነው። ስለዚህ «እኔ ከሞ ትኩ፣ ...» የሚል ሰው ካልሆነ በቀር ነገን ለሚያስብ ሰው አፉ እንዳመጣ ሊናገር ግድ የለሽ ሆኖም ሊኖር አይችልም። አርቆ የሚያስብና ከታሪክ የሚማር ትውልድ ዛሬም እንደ ዳዊት «ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ሶበ ይሄልው አበው ኅቡረ» እያለ መመ ኘቱ፣ መጸለዩ፣ በሚችለው መድከሙ አይቀሬ ነው።

አበው እንደሚሉት ላለፈ ክረምት ቤት ባይሠራም በክረምቱ የተጎዳው ቤት ግን የፈረሰው መጠገኑ፣ የወደቀው መነሣቱ የላላውና የወላለቀውም መቃናቱና መጥበቁ ወደ ቀደመ ክብሩም መመለሱ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። የተጎዳው ቤት ካልተጠገነና ወደቀደመ ሁኔታው ካልተመለሰ ግን እንኳን ሌላ ተጨማሪ ክረምት ሊያልፉበት ቀርቶ በጋውንም አያስቀምጥም። በቀን የፀሐይ ሀሩር፣ አሞራ፣ ወፍ፣ በሌሊትም ብርዱና ቁሩ፣ አራዊቱም ዕረፍት ይነሣሉና። እንደዚሁም ሁሉ ልዩነቶች በጊዜያቸው ካልተ ፈቱ በቀን አእዋፍ . በሌሊት አራዊትን አስጠግተው ምእመናንን ለሃይማኖት ዝለት እና ለምግባር ውድቀት ውለው አድረውም ለሌላ የከፋ ነገር አሳልፈው መስጠታቸው አይቀሬ ነው። ስለዚህ ለመፍትሔው ማሰብን መጨነቅንና መጸለይን የሚቀድም ሌላ ነገር ሊኖር አይችልም።

በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክም ሆነ በኢትዮጵያዊነታችን ችግሮችን በውይይት የመፍታት የዳበረ ልምድ አለን። በዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት በደብረ ምጥማቅ ጉባኤ የተፈታው ሰንበትን የተመለከተው ክርክር ለዚህ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። በአንድ ሰንበት እና በሁለት ሰንበት ጉዳይ የተጧጧፈ ክርክርና ልዩነት ተፈጥሮ ቢቆይም ንጉሡ መድረኩን ፈጥረው ለውይይት ሲጠሩ ግን ሁሉም በደስታ ተቀብለው ችግራቸውን ፈትተው የቤተ ክርስቲያንን አንድነት አጽንተዋል። ግብጻዊው ጳጳስ በጣል ያን ወረራ ሸሽተው ሲሔዱ ኢትዮጵያውያን ኤ'.ስ ቆጶሶት ከመካከላቸው መርጠው ሊቀ ጳጳስ በመሾማቸው ምክንያት የግ ብጽ ቤተ ክርስቲያን የፈጸመችው ውግዘትም በውይይት ተፈትቷል። ታዲያ ይህ ሁሉ ተጨባጭ ልምድ ያላት ቤተ ክርስቲያን ዛሬ በልዩነት እንዴት ትቀጥላለች? ትላንት መወያየትን የምታውቅ ዛሬ እንዴት ይቸግራታል? ችግሮች በተፈለገው መጠን መኖራቸው መፍትሔውን ሊያርቀው አይችልም። እንዲያውም ወደፊት ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር በር የሚዘጋ መፍትሔ በማስቀመጥ ቤተ ክርስቲያንን መጥቀም በታሪክም ተወቃሽ ከመሆን መትረፍና ተመስጋኝ የሚያደርግ ሥራ መሥራት ይገባል።

ፍጹሙና እውነተኛው መፍትሔ ደግሞ ይቅርታና ሥርየት ብቻ ነው። ከሰዎች ጋር ያለውን በይቅርታና በዕርቅ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን በንስሐና በሥርየት ዘግቶ መጭውን ሕይወት በአንድነትና በፍቅር መጓዝ ያስፈልጋል። የአገር ሽማግሌዎች፣ የአድባራትና የገዳማት አለቆች፣ ምሁራንና ወጣቶች፣ ወንዶችና ሴቶች፣ ልጆችና ዐዋቂዎች በአንድነት አሳብና በአንድ መንገድ ላይ መሆን የመጀመሪያው አስፈላጊ ነገር ነው። በውጭ አገር ያለው በአገር ውስጥ ካለው ወገኑ ጋር በመሆን ለሥርየት መዘጋጀት ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ እያንዳንዳችን በልባችን ያለውን ክፋት በመተው ይቅር በማለትና ይቅርታ በመጠየቅ ሊጀመር ይገባዋል። ከዚህ በኋላ በአስተዋይ ሽማግሌዎች አማካኝነት ልዩነቶች እንዲፈቱ መጣር ያስፈልጋል።

ሥርየት የማይፈታው ችግር የለም። ነገሮች አንድ ቦታ ላይ እንደሚጀመሩ ሁሉ አንድ ቦታ ላይም ሊቆሙ ይችላሉ። ጥ ፋ ትና በደል ከአዳም ጀምሮ አለ። ሁልጊዜም የሚፈታው ግን በይቅርታና በሥርየት ነው። ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥ ሮስ «ጌታ ሆይ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት ? እስከ ሰባት ጊዜን ? » ባለው ጊዜ ጌታ «እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም» ያለው ይቅርታና ሥርየት በቁጥርና በጊዜ የማይወሰን ሁልጊዜም የሚፈጸም በመሆኑ ነው። ማቴ18:21 ስለዚህ አሁንም ለውይይትና ለሥርየት ጊዜ አለ። ልዩነቶችን ውይይት ያቆማቸዋል፣ ይቅርታ ይፈታቸዋል፣ ሥርየትም በአንድነት ያጸና ቸዋል። ይልቁንም ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለን ችግር ያለ ሥርየት ልንፈታው አንችልም። ሥርየትን ኑዛዜ፣ ኑዛዜንም ውይይት ይቀድማቸዋል። ውይይት ከሁሉም ይቅደም እንጂ የመጨረሻውን «ዕቅበትም» የሚወስነው እርሱው ነው። ስለዚህ እንደ ጸሎታችን እንደ ዕለት ተዕለት ሕይወታችን ያለፈውን በይቅርታ ፈትተን ለሚመጣው ደግሞ ችግሮቻችን የምንፈታ ባቸውን መንገዶች ቀይሰን ወደ አንድነታችን መፍጠ ን ይጠበቅብናል። አባቶች ሆይ ስትናዝዙን የምንሰማውን «ለዘኀለፈ ሥርየት ወለዘይመጽእ እቅበት»ን በዚህ ጉዳይ ላይ ስትተገብሩ ማየትን ሁሉም ይጠብቃልና።

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር***

*Mahibere Kidusan©2005, All Rights Reserved*
***አስተያየት ለመስጠት:*** *webmaster@eotc-mkidusan.org*